# የ፳ ዓመት ሐዋርያዊ ጉዞ በምዕራብ አውሮፓ

## ከ፲፱፻፸፭-፲፱፻፺፭/ 1983-2003

በዘመነ አዝማናት የተለያየ የታሪክ ሂደት ስለአለ፣ ዓለም ከተፈጠረ፣ ዘመን ከተቆጠረ ጀምሮ የተፈጸሙ ድርጊቶች ሁሉ፣ አብዛኛዎቹ በዓመታት ተወስነው፣ ተመድበውና ተቀምረው ይገኛሉ። በዚህ አጭር መግቢያ ላይ ለማለት የምፈልገው በኮለኝ የደብረ ሰላም ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ከተቋቋመ በኋላ በጀርመንና በሌሎቹም የአውሮፓ አገሮች የተካሄደውን የ፳ኛውን ዓመት ሐዋርያዊ ጉዞ ለማዘከር ያህል ነው። ያለፈውን ያላስታወሰ ለዛሬ፣ ዛሬንም በሥራ ያልተረጎመ ለነገ ሊሆን ስለማይችል፣ ትናንት፣ ዛሬና ነገ በሚል ቀመራዊ ይዘት ተከፋፍለው ያሉ ሦስት ሁኔታዎች ለእልፍ አእላፍ ድርጊቶች መሠረታውያን ድንጋጌዎች ናቸው። የዚህም ጽሑፍ ዓላማ በእነዚህ ድርጊቶች ዙሪያ ያተኮረ ነው።



ለ፸/70/ ዓመታት ያህል በስደት ሀገር በባቢሎን (በአሁኑ ኢራቅ) የነበረ እስራኤላዊ ምርኮኛ ዕዝራ ሱቱኤል „እስኩ ጸውዓ ለዕለት እንተ ትማልም ለፈት "እስኪ ለፈችውን የትናንትናዋን ቀን ጥራት በማለት ያለፈውን ጊዜ ማስታወስ እንዳለብን ያስገነዝበናል።ያውም በባዕድ ሀገር፣ በስደት ኑሮ፣ ለምን? ለማን? ማን? ንዴት? የሚል ቃለ መጠይቅ ከተጨመረበት የድርጊቶች ሂደት ግልጽ ይሆናል።በእርግጥ ሃያ ዓመት ይህን ያህል ሩቅ ዘመን ሁኖ ጥልቅ ጥናታዊ ስሌት የሚያስፈልገው ባይሆንም፣ ከዓላማው ክቡርነት፣ ከተፈጸመውም ዝክረ ነገር የተነሣ፣ በውስጡ ለነበሩበትና ላሉበት ሁሉ ጠመዝማዛ ጉዞ ነበር። አንዳንድ ጊዜማ የጥንቷን ቤተ ክርስቲያን አባቶች የሕይወት ታሪክ መላልሰን ለማንበብ የተገደድንበት ጊዜ በቀላሉ የሚገመት አልነበረም። ቸሩ አምላካችን ግን „ኅሊና ያሰበውን፣ አእምሮ ያመላለሰውን፣ ኩላሊት ያጤሰውን" በግልጽ የሚያውቅ በመሆኑ ስንደክም አበርትቶናል። ስንወድቅ አሥንሥቶናል። ተስፋም ስንቆርጥ በቅዱስ መንፈሱ አጽናንቶናል። እንባችንን አብሷል። የልባችንንም ቁስል አድርቋል። በመከራ ብዛት፣ ጸጋ እንደሚበዛለት፣ (፪.ቆሮ. ፲፪፣ ፯-፲) በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ አንደበት የተነገረለት፣ ምርጥ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በላከው በሁለተኛው መልእክቱ በም.፬ በቁ. ፱. ላይ *„በሁሉ እንገፋለን እንጂ አንጨነቅም። እናመነታለን እንጂ ተስፋ አንቆርጥም። እንሰደዳለን እንጂ አንጣልም፣ እንወድቃለን እንጂ አንጠፋም።"* ሲል የተናገረው ኃይለ ቃል ዕለታዊ መመሪያችን ከሆነ ፳ ዓመቱን አስቆጥሯል። ከምንም ተነሥተን በእግዚአብሔር ቸርነት፣ በመልአኩ በቅዱስ ሚካኤል ተራዳኢነት ከዚህ ደርሰናል።

በውጭ ሀገር እንደ እንጉዳይ ብቅ ብቅ ካሉት ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት መካከል አንዱ፣ በጀርመን የተቋቋመው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ነው። ስለምን ቢባል በሀገራችን በኢትዮጵያ የአመጽ ሰደድ ተቀጣጥሎ፣ እልፍ አእላፍ፣ ትእልፊተ አእላፍ የሆኑ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ለስደት፣ ለመከራና ለውርደት ሲጋለጡ፣ አጽናኝ፣ መካሪና አስተማሪ ማስፈለጉ አንድና ሁለት አልነበረውም። ታዲያ በዚህ ጊዜ ነው፣ በመንፈሳዊ ትምህርት ገበታ ላይ የነበሩ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች „ለምን ቤተ ክርስቲያን አናቋቁምም" በሚል መንፈሳዊ ቅንዓት በመነሣሣት፣ ከምእመናን ጋር ውይይት በማድረግ ጽንሰ ሐሳቡን ለመድረክ ያቀረቡት። ለሁለት ዓመታት ያህል በማኅበር መልክ መንፈሳዊ ትምህርት ሲሰጥ፣ በቅድስት ማርያም ስም የጽዋ ማኅበር ሲጠጣ፣ ዓበይት በዓላት ሲከበሩ ከቆዩ በኋላ፣ ወደ አንድ የቤተ ክርስቲያን ተቋም ለመለወጥ አንድ አስተባባሪ ኮሚቴ ተቋቋመ።

ከዚህ ላይ አንዳንድ የማስታውሰውን በአጭሩ ብገልጥ መልካም ይመስለኛል። በምድረ ኢትዮጵያ „ነጭ ሽብርና ቀይ ሽብር“ ተፋፍሞ እንዳበቃ፤ ፲፱፻፹፪ እና ፲፱፻፹፫ ዓ. ም. /1982-1983/ ላይ የደርግ ክንድ ገና ያፈረጠመበት ጊዜ በመሆኑ፤ ቤተ ክርስቲያን እንድናቋቁም ይፈቀድልን ዘንድ ለመንበረ ፓትርያርክ ያቀረብነው ጥያቄ መልስ እንዳያገኝ „ቄሱና ዲያቆኑ የንጉሡን ፎቶግራፍ ሰቅለው ይጸልያሉ። የሚያካሂዱት ፀረ አብዮት ነው። የእናት ሀገር ጠላቶች ናቸው።“ የሚል በራሪ ወረቀት እንዲበተን ከመደረጉ ሌላ፤ ለመንበረ ፓትርያርኩ እንዲደርስ ይደረጋል። በሲኖዶስ ስብሰባ ቀርቦ ከተነበበ በኋላ፤ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ „ነገሩን ሰማነው፤ ጸሐፊው ማን ይባላል? አድራሻስ አለው?“ የሚል ጥያቄ ሲያቀርቡ፤ „ስምና አድራሻ የለውም“ የሚል መልስ ያገኛሉ። ወዲያው „ይፈቀድላቸው“ የሚል አባታዊ ትእዛዝ ያስተላልፋሉ። በአሁኑ ጊዜ በውጭ ሀገር ኗሪ የሆኑት፤ በዚያን ጊዜ የጠ/ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ የነበሩት ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው በቁጥር 1720/6590/75 ታኅሣሥ ፲፯ ቀን ፲፱፻፹፪ ዓ.ም./26.12.1982/ በጻፉት ደብዳቤ፤ ቤተ ክርስቲያን ለማቋቋም ከቅዱስ ሲኖዶስ መፈቀዱን ገለጹልን። እኛም ለሁለት ዓመት ያህል እንጠባበቅ ስለነበር፤ ፈቃድ ተገኝቶ ታቦተ ሚካኤልን ለማስገባት ሽርጉዱ፤ መንፈሳዊው ደስታ እንደቀጠለ፤ „ደስ ብሎናል ደስ ይበላችሁ“ ከሚል ደብዳቤ ጋር ከቤተ ክህነት የተላከው ደብዳቤ ወደ ጀርመንኛ ከተተረጎመ በኋላ ወደየቦታው ሲበተን „ያልጠረጠረ ተመነጠረ“ እንደሚለው ሆነና በደብዳቤው ይዘት ውስጥ „በመንግሥት ተፈቅዷል“ የሚል ስለአለበት፤ በግልባጩም ያን ጊዜ ቦን የነበረው ኢምባሲ እንዲያውቀው ስለተደረገ፤ ተቃውሞው በመላው ጀርመንና በመላው አውሮፓ ተዳረሰ። ዛቻና ጥላቻ እየተስፋፋ ሄደ። ከጠ/ቤተ ክህነት የመጣው ደብዳቤ „በመንግሥት ተፈቅዷል“ ያለበት ምክንያት ቤተ ክርስቲያኑን ለማቋቋም የተነሡት ግለሰቦች በፀረ አብዮት ካምፕ ውስጥ ተመዝግበው፤ በደርግ የጸጥታ ክፍል ውስጥ ጉዳዩ ደርሶ ስለነበር፤ „የእናንተ ነገር ተለይቶ ታውቋል፤ በነገሩ የላችሁበትም“ ለማለት በቅን ልቡና የተጻፈ ነበር። በደብዳቤውም ውስጥ በጊዜው የደብዳቤ መደምደሚያ ሆኖ ያገለግል የነበረው „ ኢትዮጵያ ትቅደም“ የሚለው መፈክር ስለነበረበት፤ ተቃውሞው ሊያባራ አልቻለም። እንዲያውም ቄሱና ዲያቆኑ እንደእየ መዓርጋቸው „የደርግ ኮሎኔልና ሻለቃ“ ሁነው መዓርግ ተሰጣቸው። በተለይም ሁለቱም መንፈሳዊ ትምህርታቸውን የተከታተሉት በድሮው ሶቬየት ኀብረት፤ በሌኒንግራድ፤ በአሁኑ ሩሲያ በሴንትስ ፔተርስቡርግ መንፈሳዊ አካዳሚ ውስጥ ስለነበረ፤ ለሰሚ ጆሮ መጣፈጡ አልቀረም። ለመጀመሪያ ጊዜ አንድ እሑድ ቀን አድማ ተካሂዶ፤ ሁልጊዜ ይመጡ የነበሩት ወንድሞችና እኅቶች ሳይመጡ ቀሩ። ታዲያ ቄሱና ዲያቆኑ ሲነጋገሩ „ምእመናኑ ዛሬ አልመጡም፤ ስብከት ያስፈልጋል እንዴ!“ ይላል ከሁለቱ አንዱ፤ ሁለተኛው ቀጠል አድርጎ፤ „እኛው ሁለታችን እንሰባበክ“ ይልና ነገሩ ከዚህ ላይ በውል ይቋጫል። ሁለቱም በአንድ ላይ በጸሎት ላይ እንዳሉ፤ አቶ በሪሁን ጌታቸውና ወ/ሮ ኤልሳቤጥ ተፈራ ከካርልስሩሄ፤ አቶ ብሥራት ደምሴ ከዳርምሽታት ፭ ኪሎ ሜትር ያህል አቋርጠው ወደ ሃይደልበርግ ይመጡና፤ ከሁለት ወደ ስድስት ቁጥር፤ የቄሱም ቤተ ሰብእ ሲጨመር ወደ ስምንት ነፍስ ከፍ አሉ። በዕለቱም ከማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ፲፰፤ ከቁጥር ፲፱-፳ ያለው ተነቦ „ከእናንተ ሁለቱ በምድር በማንኛውም በሚለምኑት ነገር ቢስማሙ በሰማያት ካለው ከአባቴ ዘንድ ይደረግላቸዋል። ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁና።“ የሚለው ተብራርቶ ትምህርት ከተሰጠ በኋላ፤ ጸሎቱ እንዳለቀ፤ ስምንቱ ነፍስ በአንድ ላይ ጸበል ጸዲቅ ቀምሰው፤ የሰንበት አፋቸውን አድፈው ሲለያዩ „የሳምንት ሰው ይበለን“ በማለት በየጊዜው ለመገናኘት ቀጠሮ ይዘው ተለያዩ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አዳዲስ መልክ፤ መታየቱ፤ ተሳላሚ መምጣቱ አቋርጦ አያውቅም። በዚህ ፳ ዓመት ውስጥ የተፈጸመው „ እገጭ እገው“ ሁሉ ቢዘረዘር ራሱን የቻለ ገድለ ሐዋርያት ይወጣዋል። አለበለዚያም አንድ የታሪክ ድርሳን መድበል ነው።

የኮለኝ ደብረ ሰላም ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን የዛሬ ፳ ዓመት በወርኃ ትንሣኤ በዘመነ ሉቃስ ግንቦት ፳ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ. ም./15.05.1983/ በዳግማዊ ትንሣኤ በዓል በዚያን ጊዜ የጅቡቲ ሊቀ ጳጳስ በነበሩት በአቡነ ኤልያስ እጅ ቤተ ክርስቲያኑ ተባርኮ፤ የቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ተቋቋመ። በክብረ በዓሉ ላይ የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ተጠሪዎች ተገኝተዋል። ከእነርሱም መካከል በዚያን ጊዜ በሎንዶን የኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ. ኃላፊ አባ አረጋዊ ወልደ ገብርኤል፤ በኋላም የአውሮፓ ጳጳስ የነበሩት አቡነ ዮሐንስ፤ እንዲሁም በዚያን ጊዜ የሰሜን ኮለኝ አውራጃ ሱፐርኢንትንደንት፤ በአሁኑ ጊዜ የጀርመን ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን ም/ቤት ሊቀ መንበር ማንፍሬድ ኮክ ይገኙበት ነበር። በዕለቱም ለሁለት ሕፃናት ጥምቀተ ክርስትና ተፈጽሞላቸዋል። ምንም እንኳ በዓሉ ሞቅ ደመቅ ያለ ቢሆንም፤ በዜና የመገናኛ አውታሮች ከፍተኛ የዜና ሽፋን ቢሰጠውም፤ አንዳንድ ወገኖች የቤተ ክርስቲያኑን መቋቋም፤ የእኛንም ስም በማጥፋት፤ የተቃውሞ ወረቀት መበተናቸው አልቀረም። እንዲያውም በበርሊን ሚሲዮናዊ ድርጅት የምሥራቅ አፍሪካ ክፍል ኃላፊ የነበሩት ዶ/ር ጉናር ሃሰልብላት „ ኢትዮጵያ ውስጥ ቤተ ክርስቲያን እየተዘጋ፤ ከዚህ እንዴት ይከፈታል?“ በሚል „አመክንዮ ምክንያት“ የተቃዋሚዎች ደጋፊ ከመሆናቸውም ሌላ፤ ድርጅቱ በሚያሳትመው መጽሔት ተቃውሚቸውን ገልጸዋል።

በዘመነ ደርግ በቅድስት ሀገር በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት ሊቀ ጳጳስ ሁነው ተሹመው የነበሩት አቡነ ማትያስ በመጀመሪያ ወደ እንግሊዝ ሀገር፤ ከዚያም ወደ አሜሪካ ተሰደዱ። መቀመጫቸውን ዋሽንግተን ውስጥ ካደረጉ በኋላ „የስደት ቤተ ክርስቲያን" አቋቁማለሁ በለው ተነሡ። የእኛ ቤተ ክርስቲያን እንዳይቋቋም፤ ከተቋቋመም በኋላ በሁለት እግሩ እንዳይቆም የመሰናከል አሽከላ ከዘረጉት ወገኖች ጎን ተሰለፉ። በጽሑፍና በቴፑ ከሚያደርጉት ተቃውሞ ሌላ፤ ቤተ ክርስቲያኑ በተቋቋመ ባመቱ በ፲፱፻፸፮ ዓ. ም/1984/ የእኛ ማዕከል ወደአለበት ወደ ኮለኝና ወደ ሃይደልበርግ በመምጣት እኛን „ኮንነው፤" ተቃዋሚዎችን „አጽድቀው" ተመለሱ። እንዲያውም ከመንግሥት የፖለቲካ ሰዎችና ከቤተ ክርስቲያን ኃላፊዎች ጋር በመገናኘት ለእኛ የሚደረገው ትብብር እንዳይቀጥል የተቻላቸውን ያህል ለማድረግ ሞክረዋል። ሆኖም ደርግ ከወደቀ በኋላ „ከምንታዌ ወደ ተዋሕዶ" ተመልሰው የቅዱስ ሲኖዶስ አባል ሁነዋል። ቤተ ክርስቲያናቸውም ከመንበረ ፓትያርኩ ጋር ግንኙነት ሰለአለው የአንዲት እናት ቤተ ክርስቲያን አካል ነው። በጀርመን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንስ? ያልን እንደሆን፤ በደርግም ጊዜ ሆነ፤ አሁንም የአንዲት እናት ቤተ ክርስቲያን አካል ናት። መንግሥት በተለወጠ ቁጥር የሚለወጥ „ሰው ሥራሽ" ቤተ ክርስቲያን አያስፈልገንም። መሰንበት መልካም ነው፤ ሰው ሠራሹ ደርግ ተገርስሶ፤ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ግን ከአንድ ወደ አራት አድጋ ለማየት በቅተናል። በዚህም ዓመት የአምላካችን ቅዱስ ፈቃድ ከሆነ የሽቱትጋርትና የንርንበርግ የሰንበት ት/ቤት ማኅበራት ወደ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ይሸጋገራሉ። እንግዲህ ፮ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ይኖሩናል ማለት ነው። ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያናችን እንደ ግለሰቦች ፈቃድ የምትመራ ሳይሆን፤ በቀኖና ቤተ ክርስቲያን የምትመራ መሆኗን መገንዘብ ያስፈልጋል። ይህማ ካልሆነ በሺህ፤ በሺህ ከሚሰነጠቁት ከፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት በምን ትለያለች።?



ከዚህ በላይ የተገለጸው እስከ ደርግ መውደቅ ድረስ ያለው ሁኔታ ጠቅለል ባለ መልኩ ነው። መቸም እንዳ ለመታደል ሁኖ አንድ ሥር ዓተ ምንግሥት ተለውጦ ሌላ ሲተካ የረገበው ይወጠ ራል፤የተወጠረው ይበጠሳል። የኢሕአዴግ መንግሥት በደ ርግ ቦታ ሲተካ ደግሞ፤ ሌላ አለመግባባት አቆጠቆጠ።እን ዲያውም አቡነ ኤልያስ ከስ ዊድን፤ አቡነ ይስሐቅ ከአ ሜሪካ ወደ ኮለኝ መጥተው፤ ከግንቦት ፬ እስከ ፮ ቀን ፲፱፻፹፯/12.-14.05.1995/ ዓ. ም. በተደረገ ስብሰባ፤ በጀርመን ያለችው ቤተ ክርስ ቲያን ከእናት ቤተ ክርስቲ ያን የተለየች መሆኗን „ባርከው" ተከታዮቻቸውም የቤተ ክርስቲያኒቱ የሆነውን ሁሉ እንዲረከቡ አዘው ተመልሰዋል። እነሱርም „በኮለኝና በአካባቢዋ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ የቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ" በማለት በራሳቸው ሥልጣን ሹምት ከተሿሿሙ በኋላ፤ ከቤተ ክርስቲያናችን በኩል የሕግ እርምጃ ሰለተወሰደ፤ ይዘውት የነበረውን ስም ለመተው ተገደዋል። „ፓትርያርክ እያለ ፓትርያርክ ለምን ይሾማል" ለሚለው ጥያቄ „ስህተት ሲደጋገም" በሚለው ርእስ ውስጥ በሰፊው የተዘረዘረ ስለሆነ በዚህ የመግቢያ ጽሑፍ ውስጥ ወደዝርዝር ጉዳይ መግባት አያስፈልግም። አሁንም ያ የፈተና ጊዜ አልፎ፤ ፳ኛውን ዓመት ለማክበር በመብቃታችን እጅግ ደስ ይለናል። ለአምላካችንም ጥልቅ ምስጋናን እናቀርባለን። ሁኖም አንዳንድ ጊዜ ማጉረምረማችን አልቀረም። በውስጡ ያለፍንበትና ያለንበት ሁሉ፤ „ ሰላምን እንሻለን፤ ፍቅርንም፤ እንከተላለን፤ የቤተ ክርስቲያንንም መሠረት እንጥላለን፤ ለሀገር፤ ለወገን መልካም ምሳሌ እንሆናለን፤ ሕዝብ እናጽናናለን፤" ብለን ተነሥተን፤ ያለ በቂ ምክንያት አለመግባባት ሲከሠት፤ እርስ በእርስ ተጠላልፎ ለመወደቅ ስንሯሯጥ፤ ማዘናችን አይቀሬ ሁኖብናል። ሆኖም የጌታ ወንድም ሐዋርያ ያዕቆብ በምዕራፍ ፩፤ በቁጥር ፪-፫፤ „ ወንድሞቼ ሆይ የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንዲያደርግላችሁ አውቃችሁ፤ ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቁጠሩት።" ሲል የተናገረው፤ የክርስቲያኖች ሁሉ መመሪያ ሊሆን ይገባዋል።

እኛም ተጠቅመንበታል። ከአዘነው ወገናችን ጋር አብረን አዝነናል። ከተደሰተውም ጋር አብረን ተደስተናል። ችግሩን ብቻ ሳይሆን፤ ጸጋውንም ተቀብለናል።


በጀርመን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በመቅረዝ ላይ ያለች ሡብራት በመሆኗ፤ ከማብራትና ከማንጸባረቅ „የሰማይ መላእክትና የምድር ሠራዊት ሊጋርዷት፤ የገሃነምም ደጆች ሊያነዋውጧት“ አልቻሉም። በተለይም „እኔ የአጵሎስ፤ አንተ የኬፋ፤ ያ የጳውሎስ“ የሚሉ ኃይሎች መቅረዟን ማወዛወዛቸው አልቀረም። ነገር ግን የቤተ ክርስቲያን መሠረት ኢየሱስ ክርስቶስ፤ መሪዋም መንፈስ ቅዱስ በመሆኑ ማዕበልና ሞገድ ባለበት ሁሉ መልሕቋን ጥላ ትገኛለች። ቤተ ክርስቲያን በድቡሽት ላይ ያልተመሠረተች በመሆኗ ማዕበሉና ሞገዱ ቢጸና፤ ጎርፉም ቢያጥለቀልቅ አልወደቀችም። መሠረቷም አልተናወጠም። እንዲያውም ማዕከሏን በፌደራል ሪፑብሊክ ጀርመን ውስጥ አድርጋ በሌሎች የአውሮፓ ሀገሮች፤ በሆላንድ፤ በቤልጅግ፤ በፈረንሳይ፤ በኢጣሊያ፤ በስዊዘርላንድ፤ በኦስትርያ፤ በቸክና በስዊድን ሐዋርያዊ ጉዞ በማድረግ መንፈሳዊ አገልግሎት ለማበርከት ችላለች። በዚህ ፳ ዓመት ውስጥ በተለያዩ፤ እጅግ ብዙ በሆኑ በጀርመን ከተማዎች መንፈሳዊ አገልግሎት፤ ተሰጥቷል። ዐውደ ጥናት ተካሂዷል። ቤተ ክርስቲያኗ „ከፈሪሳዊነት ጠባይ“ የተላቀቀች በመሆኗ፤ ምእመናን ብቻ ወደ እርሷ እንዲመጡ የምትጠብቅ ሳይሆን፤ እርሷም እነርሱ ወደ አሉበት የምትሄድ ስለሆነ፤ ለሌሎችም መልካም አርአያ እንደሚሆን ይታመናል።

ከዚህ ቀጥሎ በሁለት ክፍል በመክፈል በጀርመንና ከጀርመን ውጭ ቤተ ክርስቲያን ለማቋቋም የተደረገውን ጥረት መመልከት ይቻላል።

<u>ክፍል ፩ በጀርመን ሀገር</u>

<u>፩/ የኮለኝ ደብረ ሰላም ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን</u>

ስለ ኮለኝ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ከሞላ ጎደል እስካሁን ስለተነገረ ወደ ዝርዝር ሁኔታ መግባት አያስፈልግም። ከዚህ ላይ መገለጽ የሚገባው ነገር ቢኖር፤ ራሱን የቻለ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ከብዙ ድካምና ጸሎት በኋላ ስለተገኘ እንደ ኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ. ቀኖና መሠረት አምልኮተ እግዚአብሔር መፈጸም ተችሏል። ፫ በር ያለው ቤተ መቅድስ በሥዕል እንዲዋብ፤ መንበረ ታቦት እንዲኖረው ተደርጓል። ደጀ ሰላምም ስለአለው፤ ፳፬ ሰዓት መጠቀም ይቻላል። ለ፲፪ ዓመታት ያህል ከእኛ ጋር ቤተ ክርሰቲያኑን ይጋሩ የነበሩት ቄስ ዩርገን ሞካ ቁልፉን ባስረከቡን ጊዜ የተናገሩትን፤ ከዚህ ላይ ማስታወስ ምስክርነት ነው። „ጸሎታችሁ ተራራ ይንዳል“ ነው ያሉት። አሁንም ክብርና ምስጋና ለኃያሉ ጌታ ይሁን።



<u>፪/ በሙኒክ የደብረ ብሥራት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን</u>

በየቦታው ቤተ ክርስቲያን ማቋቋም አማራጭ የሌለው ግዴታ መሆኑ የታወቀው ከዛሬ ፳ ዓመት በፊት ነበር። ነገር ግን ለካህን የሚሆን በጀት ባለመገኘቱ ለብዙ ጊዜ በሥራ ሳይተረጎም ቆይ ቷል። በ፲፱፻፹፫ ዓ.ም. /1991/ ላይ ለአንድ ካህንና ለአንድ ዲያቆን የሚሆን በጀት በመገኘቱ፤ ቄስ መስ ፍን ገብረ ማርያም ከኢየሩሳ ሌም መጥተው በቅስና፤ ዲያ ቆን ዘለዓለም መንግሥቱ በዲቁና ተመድበው፤ የቋሚ ካህናት ቁጥር ከአንድ ወደ ሦስት ከፍ እንዲል ተደረገ፤። ቋሚ ካህን በመገኘቱ፤ ኅዳር ፲፱ ቀን ፲፱፻፹፮/28.11.1993/ ዓ. ም. በጀርመን ሀገር የመጀመሪያው ቤተ ክርስቲያን በተቋቋመ በ፲ኛው ዓመት በሙኒክ የደብረ ብሥራት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ተቋቋመ። ዝርዝር ሂደቱንና ዕድገቱን የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በሚለው ውስጥ መመልከት ነው።

፫/ በፍራንክፈርት የቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን

በፍራንክፈርትና በአካባቢው ብዙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታዮች እንደሚኖሩ የታወቀ ነው። ሰለዚህም በኮለኝ ቤተ ክርስቲያን ለማቋቋም ጥረት የተደረገውን ያህል በፍራንክፈርትም ቤተ ክርስቲያን ለማቋቋም ብዙ ጥረት ተደርጓል። ምንም እንኳን ቋሚ ካህን ኖሮ ቤተ ክርስቲያን ለማቋቋም ባይቻልም፤ እንደ ኮለኙ ሁሉ በየጊዜው መንፈሳዊ አገልግሎት ይሰጥ ነበር። ይህንንም ከግምት ውስጥ በማስገባት በዕለተ ትንሣኤ እንኳን ሳይቀር፤ ቤተ ክርስቲያን ዘግቶ በመሄድ የ፲፱፻፸፮/1984/ ዓ. ም. የትንሣኤ በዓል ከሰሚናር ጋር እንዲከበር ተደርጓል። በበዓሉም ላይ ከ፯፻-፰፻ የሚገመት ሰው ነበር። ውጤቱ ግን አመርቂ አልሆነም። „እኔ የዚህ፤ አንተ የዚያ“ በሚሉ፤ የክርስትና ሃይማኖት ውሳጣዊ ጥልቀት ባልገባቸው ወገኖች የተሰበሰበው ተበተነ። የቀረበውም ራቀ። ከእናት ቤተ ክርስቲያን በመለየት ቀኖናዊ ባልሆነ መንገድ „የኢትዮጵያ ስደተኞች የመድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን“ በሚል ስም ቤተ ክርስቲያን እንዲቋቋም፤ አባ ዘመንፈስ ቅዱስ ወልደ ሥላሴም ከሱዳን እንዲመጡ ተደረገ። አሁንም በኢትዮጵያ የሥርዓተ መንግሥት ለውጥ ሲደረግ፤ አባ ዘመንፈስ ቅዱስ ወልደ ሥላሴ ሕጋዊ ቤተ ክርስቲያን እንዲቋቋምላቸው በራሳቸውና በምእመናኑ ስም ጠየቁ። በአውሮፓ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ በነበሩት በብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ሐምሌ ፩ ቀን ፲፱፻፹፯ /08.07.1995/ ዓ. ም. ቤተ ክርስቲያኑ ተባርኮ ታቦተ ማርያም እንዲገባ ተደርጓል። በአሁኑም ጊዜ አባ ሲራክ ወልደ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያኗን በመምራት ላይ ናቸው፡፡ አሁንም ሂደቱንና ዕድገቱን የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በሚለው ውስጥ መመልከት ይቻላል።

፭/ በበርሊን የቅዱስ አማኑኤል ቤተ ክርስቲያን

በበርሊን ቤተ ክርስቲያን ለማቋቋም ታስቦ፤ ለ፲፪ ዓመታት ያህል መንፈሳዊ አገልግሎት ሲሰጥ መኖሩ ይታወሳል። በተለይም የበርሊን ግንብ ከፈረሰ በኋላ፤ በምሥራቅ አውሮፓ ይማሩ የነበሩ ተማሪዎች በብዛት ወደ በርሊን ከተማ መግባታቸው ይታወቃል። እንዲሁም ከሁለቱ ጀርመኖች መዋሐድ በኋላ በርሊን እንደገና የጀርመን ዋና ከተማ ሲሆን፤ የቤተ ክርስቲያኑ መቋቋም እጅግ አስፈላጊ ሁኖ ተገኝቷል። ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ ለ፫ ዓመት ያህል መደጎሚያ የሚሰጥ ድርጅት ሰለተገኘ፤ የሰሜን ወሎ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ በሆኑት በብፁዕ አቡነ ቁርሎስ ጥር ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፫ /04.02.2001/ ዓ. ም. ቤተ ክርስቲያኑ ተባርኮ ታቦተ አማኑኤል እንዲገባ ተደርጓል። አባ ብርሃነ መስቀል ተድላ ከኢትዮጵያ መጥተው ቤተ ክርስቲያኑን በማገልገል ላይ ይገኛሉ። አሁንም እንደላይኞቹ ሁሉ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በሚለው ውስጥ ዝርዝር መግለጫውን መመልከት ነው።

እስካሁን የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የተቋቋሙባቸው ቦታዎች ተገልጸዋል። ወደፊትም ቅድም ተከተላቸውን የሚጠብቁ ፯ ቦታዎች ይገኛሉ። እነርሱም፤-

፩/ ሽቱትጋርት ፬/ ኑርንበርግ
፫/ ሃምቡርግ ፭/ ካስል
፭/ ካርልስሩሄ ፯/ ዳርምሽታት
፯/ ሃኖቨር ናቸው። በነዚህ ቦታዎች የሰንበት ት/ቤትና የጽዋ ማኅበር ተቋቁመው ስብከተ ወንጌል ይሰጣል፤ ጸሎተ ቅዳሴ ይካሄዳል። የዳርምሽታት ሰንበት ት/ቤት ግን የአቋም ችግር ሰለአለበት፤ ገና መስተካከል የሚገባው ሁኔታ ከፊታችን እንደተደቀነ ነው።

**ክፍል ፪ ከጀርመን ውጭ**

ቀደም ብሎ እንደተገለጸው በሌሎች የአውሮፓ ሀገሮች ቤተ ክርስቲያን ለማቋቋም ከ፲፱፻፸፱ /1987/ ዓ. ም. ጀምሮ ከፍተኛ ጥረት ሲደ
ረግ ኖሯል።

፩/በሆላንድ ፪/ በስዊዘርላንድ
፫/በኢጣሊያ ፬/ በስዊድን
፭/ በፈረንሳይ ፮/ በቤልጅግ
፯/ በኦስትርያ ፰/ በቸክ ሲሆን፤ በሆላንድ፤ በስዊዘርላንድ፤ በኢጣሊያና በስዊድን የተደረገ ጥናት ለቅዱስ ሲኖዶስ መቅረብ ስለነበረበት፤ ያን ጊዜ የተደረገው ጥናት በዚህ ለ፳ኛው ዓመት መታሰቢያ በተዘጋጀው መጽሐፍ ውስጥ፤ እንዲታተም ስለተደረገ፤ ወደ ዝርዝር ጉዳዩ ለመግባት አልፈልግም። ከዚያው መመልከት ይቻላልና ነው። በዚያ ጥናት ውስጥ ላልተጠቃለሉት ግን የምለው አለኝ። በፈረንሳይ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እንዲቋቋም ሙከራ የተደረገው ከ፲፱፻፹፪/1990/ ዓ. ም. ጀምሮ ነው። በተለይም ወ/ሮ ሃናማሪ ማዮ፤ ወ/ሮ ብርሃኔ ነጋና ወ/ሮ የምሥራች ጌታቸው የተባሉ እንቶች የ፲፱፻፹፪ ዓ. ም. የልደት በዓል በፓሪስ ከተማ በደመቀ ሁኔታ እንዲከበር አድርገዋል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በየጊዜው መንፈሳዊ አገልግሎት ይሰጣል።የሰንበት ትምህርት ቤትም ተቋቋሟል። እንዲሁም በተደረገው እንቅስቃሴ፤ በተለይም ከ፲፱፻፹፭ /1993/ ዓ. ም. ጀምሮ በእመቤታችን

በቅድስት ማርያም ስም የጽዋ ማኅበር ተቋቁሞ፤ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ እንዲህ በቀላሉ የሚገመት አይደለም። በዚህም ዓመት የልደት በዓል በደመቀ ሥነ ሥርዓት እንዲከበር ለማድረግ ችሏል። ከጀርመንና ከሆላንድ የሄዱ መዘምራን ለበዓሉ ድምቀት ስጥተውት ውለዋል። ከ፳፫ በላይ የሚሆኑ ፈረንሳውያንም ተገኝተዋል። አንድ ስለ ቅዱስ ያሬድ ዜና ሕይወት ጥናት ያደረጉ፤ የግዕዝ ቋንቋ ተመራማሪ የሆኑ ፈረንሳዊ ምሁር ንግግር አድርገዋል። ታዲያ አሁን ያለው ጥረት ቤተ ክርስቲያኑን ማቋቋም ብቻ ነው። አስፈላጊው ንዋየ ቅድሳት ሁሉ ተሟልቶ ይገኛል። የሕዝበ ክርስቲያኑም ትብብር የሚያበረታታ ነው። እየተማረ አገልግሎት የሚሰጥ ካህን ለማግኘት ጥረቱ እንድቀጠለ ሲሆን፤ የነጻ ትምህርቱ ዕድል እንደተገኘ፤ በሥራ ይተረጎማል የሚል ተስፋ አለን።

__በኦስትርያ የቅድስት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን__

አሁንም እንደሌሎቹ ቦታዎች በኦስትርያ ቤተ ክርስቲያን ለማቋቋም ምኞቱና ጥረቱ ነበረ። በተለይም ሁለት እኅትማማቾች ወ/ሮ እንግዳሸት መለሰና ወ/ሮ ጽጌ መለሰ ከቬና ወደ ኮለኝ መጥተው የልደትን በዓል ከእኛ ጋር ባከበሩበት ጊዜ፤ ቤተ ክርስቲያን ለማቋቋም ስለሚቻልበት ሁኔታ መነጋገራችን አልቀረም። ለጥቂት ዓመት ያህል የሐሳብ ልውውጥ ስናደርግ ከቆየን በኋላ፤ በ፲፱፻፺፱ /1997/ ዓ. ም. በቬና ያሉ ክርስቲያኖች ጸሎተ ቅዳሴ እንዲካሄድላቸው ጥያቄ አቀረቡ። ነሐሴ ፲፰ ቀን ፲፱፻፺፱ /24.08. 1997/ ዓ. ም. ከፍልሰታ ጾም በኋላ፤ ለነሐሴ ኪዳነ ምሕረት ሳምንት ለመጀመሪያ ጊዜ በምድረ ኦስትርያ



ሥርዓተ ቅዳሴ ተካሄዷል። ለአንድ ሕፃንም ጥምቀተ ክርስትና ተፈጽሞለታል። የምእመናኑም ትብብር በጣም አስደሳች ነበር። በተለይም ቤተ ክርስቲያን እንዴት መቋቋም እንዳለበት ውይይት ተካሂዷል። በግንባር ቀደም ትብብር ያደረጉትን ከዚህ ላይ ማስታወስ አስፈላጊ ይመስለኛል። በዚያን ጊዜ በኦስትርያ የኢትዮጵያ አምባሳደር የነበሩት ክብርት ወ/ሮ መንበረ አለማየሁ፤ ወ/ሮ ጽጌ መለሰ፤ ዶ/ር ጌታ ሰጠኝ ዓምደ ጽዮን፤ አቶ ጀምበሩ ታየና አቶ ኃይሉ ያዛቸው ለቤተ ክርስቲያኑ መቋቋም ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል። በተለይም ለቤተ ክርስቲያኑ መቋቋም የሕዝቡን መንፈስ የቀሰቀሰው ከመስቀል በዓል ጋር ከመስከረም ፲፭-፲፯ ፲፱፻፺፩/25.-27.09.1998/ ዓ.ም. ድረስ የተካሄደው ዐውደ ጥናትና ዐውደ ትርእይት ነበር። ከጀርመንም የሄዱት የሙኒክና የጊሰን መዘምራን ለበዓሉ ድምቀት ሰጥተውት ውለዋል። ክብርት አምባሳደር ወ/ሮ መንበረ አለማየሁ፤ አያሌ የኦስትርያ ባለሥጣኖችና የአርመን ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ሜርሶፕ ክሪኮሪያን ተገኝተዋል። የኦስትርያው ካርዲናል ክርስቶፍ ሾንቦርንም የመልካም ምኞት መግለጫ አስተላልፈዋል። ለካህን የሚሆን ቋሚ በጀት ለማግኘት ባለመቻሉ የትምህርት መደጎሚያ ማፈላለጉ ግዴታ ነበር። ይሁን እንጂ አፍሮ-አስያ የተባለ ካቶሊካዊ ድርጅት የነፃ ትምህርት ዕድል ስለሰጠ፤ እየተማሩ መንፈሳዊ አገልግሎት እንዲሰጡ አባ ኪዳነ ማርያም ደስታ ወደ ቬና እንዲመጡ ተደርጓል። ከዚህም በኋላ ሚያዝያ ፱ ቀን ፲፱፻፺፩/ 17.04.1999/ ዓ. ም. የሀድያ ከንባታና የጉራጌ ጳጳስ በሆኑት በብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅ ቤተ ክርስቲያኑ ተባርኮ ታቦተ ኪዳነ ምሕረት እንዲገባ ተደርጓል።

## ልዩ ልዩ የሥራና የአገልግሎት እንቅስቃሴ

### ፩/ ስብከት በሬዲዮ

„ልበ አምላክ“ ተብሎ የሚጠራው ንጉሥ ዳዊት በ፲፫ኛው (፲፬) መዝሙሩ ላይ „ሰነፍ በልቡ እግዚአብሔር የለም ይላል። በሥራቸው ረከሱ፤ ጎሰቆሉ፤ በጎ ነገርን የሚሠራ የለም።“ ብሎ የተናገረው ትንቢታዊ ቃል በሀገረ እግዚአብሔር በምድረ ኢትዮጵያ የተፈጸመው፤ በዘመነ አብዮት ነው ብሎ መናገር ሁኔታዎችን ማጋነን አይደለም። በፀረ ኢትዮጵያና በፀረ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ከቆሙ ክፍሎች ጋር ግንኙነት ያላቸው የምሁር ቅይጥ ወጣት ኢትዮጵያውያን ከውጭ የተጫኑትን „የአምላክ ቢስነት ትምህርት“ ኢትዮጵያ ውስጥ ዘከዘኩት። በበመንበሩና በዙፋኑ ላይ አመጹ። ንጉሠ ነገሥታቸውንና ፓትርያርካቸውን ለሞት አሳልፈው ሰጡ። በጠላት ላይ አምጸው፤ ሀገር ጠብቀው ያቆዩ ጀግኖችን ያለፍርድ አስረሸኑ። የጦር መሣሪያ ያነገበውንም ከጎናቸው ስለአሰለፉት፤ የጦር መሣሪያ ድምፅ ሳይሆን፤ የወንጌል ድምፅ፤ ድመፀ ተዋሕዶ ተዘጋ። ከዘመነ ደርግ በፊት፤ በዓበይት በዓላት የኢትዮጵያ ራዲዮ ጣቢያ መስመሩን ከቅድስት ሥላሴ ካቴዳራል ጋር በማያያዝ ያስተላልፈው የነበረው መንፈሳዊ አገልግሎት፤ ዝማሬ፤ ውዳሴ፤ ቅዳሴ፤ ያሬዳዊ ሽብሸባና ትምህርተ ወንጌል ተቋረጠ። በአጠቃላይ በኢትዮጵያ የሚገኙ የመገናኛ አውታሮች የቤተ ክርስቲያንን መንፈሳዊ እንቅስቃሴ እንዳይተነፍሱ አንደበታቸው ተዘግቶ ነበር። ይህን የመሰለውን የመንፈስ ነፃነት ገፋፊ፤ መቋቋም የሚቻለው፤ በጀርመን ራዲዮ ጣቢያ በዶቼ ቬለ (Deutsche Welle) መንፈሳዊ መልእክት በማስተላለፍ መሆኑን ስለተገነዘብነው፤ በፕሮፌሰር ሃየር አማካይነት፤ ለዶቼ ቬለ የአማርኛው ክፍል ኃላፊ ለነበሩት ለፍራንክ ሌምከ ጥያቄ አቀረብን። ጥያቄውም መልስ በማግኘቱ፤ የራዲዮ ስብከት የተጀመረው ከዛሬ ፳፫ ዓመት በፊት ነበር። ያን ጊዜ ሌላ አማራጭ ስላልነበረ፤ የአምላክ ቢሶችን እኩይ ተግባር ለመናድ ተችሏል። ከኮለኝ የሚተላለፈው መንፈሳዊ መልእክት የብዙዎቹን ልብ ስለነካ፤ እጅግ ብዙ ደብዳቤዎች ደርሰውናል። እንዲያውም „ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ቤተ ክህነት ያለው አዲስ አበባ ነው? ወይስ ጀርመን ሀገር ?“ የተባለበት ጊዜ ይህን ያህል ሩቅ አይደለም። ቤተ ክርስቲያኑ እንዲቋቋም የፈቀዱት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት፤ ከጀርመን የሄዱ እንግዶችን ተቀብለው አባታዊ ቡራኬ ከሰጡ በኋላ፤ በጀርመን ስለተቋቋመችው ቤተ ክርስቲያን ሲናገሩ፤ „ይህች ቤተ ክርስቲያን እኮ የምትሠራው እኛ የማንሠራውን ነው፡!“ በለው ተናግረዋል። ከደርግ ሰዎችም „እኛ ዓመት የደክምንበትን በአንድ ቀን የሚንዱ አሉ።“ ሲሉ ተደምጠዋል። ከደረግ መውደቅ በኋላም በዓበይት በዓላት የሚተላለፈው መንፈሳዊ መልእክትና ስብከተ ወንጌል እንደቀጠለ ነው። የጀርመን ራዲዮ ጣቢያ፤ ያማርኛው ክፍል ኃላፊ ለሆኑት ለአቶ አማኑኤል በረከትና ለሥራ ባልደረቦቻቸው ልባዊ ምስጋና እናቀርባለን። አቶ ጌታቸው ደስታም ወደ ኢትዮጵያ ከመመለሳቸው በፊት በተገኘው ዕድል ሁሉ የቤተ ክርስቲያናችንን ዜና በማስተላለፍ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል። በአሉበት ምስጋናችን ይድረሳቸው።



### ፪/ የሰንበት ት/ቤት

በ፸ቱ አጥቢያ አብያተ ክርስ ቲያናት የሰንበት ት/ቤት የተቋቋመ ሲሆን፤ ከላይ እንደ ተገለጸው በ፯ ከተማ ዎችም ተቋቁሞ የመዝሙር፤ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፤ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ፤ የመ ሠረተ ሃይማኖት ትምህርት ይሰጣል። ሁኔታውም ከፍ ተኛ ትኩረት የሚሰጠው ሐዋርያዊ ተግባር ነው። „የቤተ ክርስቲያን ብርሃን„ በመባል የሚታወቀው ሐዋ ርያ ቅዱስ ጳውሎስ፤ ወጣት ተማሪውን እንዲህ ሲል ያስ ገነዝበዋል። „ነገር ግን ክፉ ዎች ሰዎችና አታላዮች እያ ሳቱና እየሳቱ፤ በክፋት እየ

ባሉ ይሄዳሉ። አንተ ግን በተማርህበትና በተረዳህበት ነገር ጸንተህ ኑር፤ ከማን እንደተማርከው ታውቃለህና፤ ከሕፃንነትህም ጀምረህ ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን፤ መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳት መጻሕፍትን አውቀሃል።" (፪.ጢሞ. ፫፤ ፲፫-፲፭) አንድ ሰው ካልተማረ አያውቅም። ምንም እንኳን የተፈጥሮ እውቀት መኖሩ ባይካድም፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርትና በቤተ ክርስቲያን ትውፊት ያልታነጸ ኦርቶዶክሳዊ ወጣት የነገይቱ ቤተ ክርስቲያን ተረካቢ ሊሆን አይችልም። የወጣቶችን ጥቅም ቀደም ብሎ የተረዱት አንድ የሮም ፓፓ „የዓለም ሕዝብ ሆይ ልጆችህን ስጠኝና፤ ዓለሙን ሁሉ ካቶሊክ ላድርገው" ነው ያሉት። የነገው ተተኪ ወጣቱ ትውልድ ነውና። የእኛም ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ትኩረት ልተሰጠው የሚገባው መዋቅር ነው። እስካሁን አቅም በፈቀደ መጠን የሚቻለውን ያህል ተደርጓል። ወደ ፊትም በበለጠ እቅድ ለመሥራት፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ አጠቃላይ የሰንበት ት/ቤት ማኅበር ተቋቁሟል። በማኅበር ደረጃ መዘጋጀታቸው ለተቀነባበረ ተልእኮ ድርሻ ይኖረዋል። የዚህንም የሥራ ውጤት በዓበይት በዓላትና በኤክስፖ ፪ ሺህ ለመረዳት ተችሏል። ከየቦታው የተወጣጡ፤ ፴ የሚሆኑ የሰንበት ት/ቤት መዘምራን በሃኖቨሩ ኤክስፖ ፪ ሺህ ላይ በመካፈል የኢትዮጵያን ብሔራዊ ቀን እጅግ አድምቀውት ውለዋል። ለብሔራዊ ቀኑ እጥፍ ድርብ ድምቀት ስለ ሰጡት ከኢትዮጵያና ከኢትዮጵያ ውጭ የመጡ የክብር እንግዶች „በዓል በዓል የመሰለው አሁን ነው።" ሲሉ ተደምጠዋል። ወጣቶች በሰንበት ት/ቤት ሥር ታቅፈው ከተንቀሳቀሱ በጀርመን ሀገር የተቋቋመችው ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያናችን የወደፊት ተስፋዋ ብሩህ እንደሆነ መተንበይ ይቻላል። ለሁሉም ግን የመንፈስ ቅዱስ አጋዥነትና የጸሎት ኃይል ሲጨመርበት ነው።

## ፫/ የጽዋ ማኅበር

አሁንም እንደ ሰንበቱ ት/ቤት ሁሉ አብያተ ክርስቲያናት በተቋቋሙባቸውና ባልተቋቋሙባቸው ቦታዎች የጽዋ ማኅበር ተቋቁሟል። የጽዋ ማኅበር ዕድሜ፤ እንደ ክርስትናው ሃይማኖት ሁለት ሺህ ዘመን ሊያስቆጥር ነው። የጥንት ክርስቲያኖች አንድ ላይ ተሰባስበው ከጸለዩና ከዘመሩ በኋላ፤ በአንድ ላይ የፍቅር ምግብ ይመገቡ ነበር። ከዚህም በመነሣት ነው፤ ከዘመናችን የደረሰው፤ ይህንንም የተቀደሰ ትውፊት የውጭ ሚስዮናውያን እነርሱ ሰለረሱት፤ የኢትዮጵያ ኦ.ተ.ቤ.ክ. ጠብቃ ስለያዘችው ብቻ፤ ብዙ ተችተውታል። ፀረ ማርያም፤ ፀረ መላእክት፤ ፀረ ሰማዕታትና ፀረ ጻድቃን ናቸውና አይፈረድባቸውም። በአንድ የጽዋ ማኅበር ዝክር ላይ ሁልጊዜ የሚነገረው ቃል „ወኩሉ ዘጸውዐ ስመ እግዚአብሔር ይድኅን" የእግዚአብሔርን ስም የጠራ ሁሉ ይድናል የሚል ነው። (የሐዋ.ሥራ ፪.፳፩) በማንኛውም ቅዱስ ወይም መልአክ ስም የሚባረከው የጽዋ ማኅበር በጌታ ስም ስለሆነ ምን ጊዜም ከጥያቄ ውስጥ የሚገባ አይደለም። ከዚህም የተነሣ፤ ቤተ ክርስቲያናችን የጽዋ ማኅበራትን ታበረታታለች። በአንጻሩም የጽዋ ማኅበራት የቤተ ክርስቲያን የአጥንት ጀርባ እየሆኑ ተገኝተዋል። አሁን በአውሮፓ የተቋቋሙት አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ በጽዋ ማኅበራት ውስጥ ያለፉ ናቸው። አሁንም ቢሆን በዓበይት በዓላትና በበዓለ ንግሥ ግንባር ቀደም በመሆን ድግስ የመደገሱ ኃላፊነት በእነሱ ትከሻ ላይ እንደ ወደቀ ነው።



## ፬/ ዐውደ ጥናት

ከዛሬ ፳፪ ዓመት በፊት ቤተ ክርስቲያን ለማቋቋም ጥረት ስናደርግ፤ የመጀመሪያው እቅዳችን አንድ ዐውደ ጥናት ማካሄድ ነበር። ዐውደ ጥናቱ ከልደት በዓል ጋር ተያይዞ የተዘጋጀ ስለነበር ዋናው ርእስ „ሰላም በምድር" የሚል ነበር፤ ከዚያ ወዲህ በተለያዩ አርእስቶች የተለያዩ ዐውደ ጥናቶች ተካሂደዋል። በተለይም በሙኒክ፤ በኑርንበርግ፤ በሽቱትጋርትና በኮለኝ የተካሄዱት „የተምሮ ማስተማር" ዐውደ ጥናቶች የወጣቱን እንቅስቃሴ ያነቃቁ ነበሩ። የዐውደ ጥናቱም ዓላማ ተምሮ ለማስተማር

ችሎታ ያላቸውን ወጣቶች ስለ ስብከተ ወንጌል፤ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ያጠናን ዘዴ፤ ሰለ ሕገ ቤተ ክርስቲያንና ሰለ ዓለም አቀፍ ክርስቲያናዊ ግንኙነት ግንዛቤ እንዲያገኙ ለማድረግ ነው። አሁንም ወደፊት ይቀጥላል። አንድ ሁኔታ ግን ግልጽ መሆን ያለበት፤ ወጭውን ለመሸፈን የቤተ ክርስቲያናችን አቅም የሚፈቅድ ሁኖ አልተገኘም። እስካሁን የተካሄዱ ሰሚናሮች ሁሉ በከፊል ከመንግሥትና ከተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት በተገኘ ገንዘብ ነበር። አሁን ያለው የቁጠባ መመሪያ፤ የነበረንን የሥራ እንቅስቃሴ እየገታው በመሄድ ላይ ነው። ሆኖም ምእመናን በሰበካ ጉባኤ አባልነት መዋጯቸውን ያለ ማቋረጥ ከከፈሉ፤ ያልተመዘገቡትም ከተመዘገቡ፤ ራስን የመቻሉ ሁኔታ ሩቅ ሊሆን አይችልም።

## ፭/ የሥነ ጽሑፍ ስርጭት

ከቤተ ክርስቲያኒቱ ጋር ፳ ዓመቱን ያስቆጠረ፤ በአማርኛና በጀርመንኛ እየታተመ የሚወጣ፤ በመጀመሪያው የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ስም የተሰየመ „ሰላማ“ የተባለ መጽሔት እንዲኖራት ተደርጓል። እንደ አስፈላጊነቱም የተለያዩ መግለጫዎች እየተዘጋጁ ለሕዝበ ክርስቲያኑ ታድለዋል። እንዲሁም የአጽዋማትና የበዓላት የቀን መቁጠሪያ እየተዘጋጀ ስለሚወጣ ከውድ ሀገሩና ከቅድስት ቤተ ክርስቲያኑ ተለይቶ በውጭ ሀገር ለሚኖረው ሕዝበ ክርስቲያን የሚሰጠው አገልግሎት ከፍተኛ መሆኑን፤ ከተጠቃሚው የሚቀርበው ምስጋና ያረጋግጣል።

## ፮/ የነፍስ አድን ጥሪ

ሀገራችን ኢትዮጵያን ድርቅ፤ ረሀብና ጦርነት መላልሰው እንዳጠቋት ከኢትዮጵያውያንና ከዓለም ኅብረተ ሰብ ኀሊና በቀላሉ የሚፋቅ ሁኖ አልተገኘም። ከዛሬ ፳፱ ዓመት በፊት በሀገራችን የሥርዓተ መንግሥት ለውጥ ተካሂዶ የተፈጸመው ግፍና ሰቆቃው፤ ረሀብና እልቂት በተለያየ ብዕር ቢጻሰስም፤ እጅግ ግዙፍ በመሆኑ ሁኔታው ሁሉ በጣም አሳዛኝና ዘግናኝ ነበር። ታዲያ የዛሬ ፳ ዓመት በምድረ ጀርመን የተቋቋመችው ቤተ ክርስቲያናችን በጽሞናና በሀዘን ብቻ ልትመለከተው አለቻለችም። በነፍስ አድን ጥሪው በመካፈል የልብስ፤ የምግብ፤ የመድኃኒትና የገንዘብ እርዳታ አድርጋለች። ለሁለተኛም ጊዜ ከበጎ አድራጊዎችና ከአብያተ ክርስቲያናት ጋር በመሆን የእርዳታ አስተባባሪ ኮሚቴ በማቋቋም፤ ጠርቀም ያለ ገንዘብ ለማሰባሰብ ችላለች። በዚህም ገንዘብ ፯ የእህል ወፍጮዎች ተገዝተው ለገዳማት እንዲሰጡ፤ ከመላኳ ባሻገር፤ ለኢትዮጵያ ኦር ኦር / ቦተ ክርስቲያን የመጀመሪያው የሆነውን የሻማ ማምረቻ ገዝታ አበርክታለች። አሁንም እንደገና ከዛሬ ፲ ዓመት በፊት በተከሠተው ረሀብ፤ የነፍስ አድን ጥሪ በማድረግ፤ ከፍተኛ ገንዘብ ተሰብስቦ፤ በእናት ቤተ ክርስቲያናችን በኩል በተቋቋመው የእርዳታ ማስተባበሪያ ኮሚሽን አማካይነት ረሀብ ላጠቃቸው ወገኖቻችን እንዲደርስ ተደርጓል። ወገኖቻችን ከዚህ የረሀብ አዙሪት እስካልወጡ ድረስ፤ ቤተ ክርስቲያናችን የመርዳት ግዴታ አለባት። አሁንም በዚህ ዓመት ለ፬ኛ ጊዜ የነፍስ አድን ጥሪ በማድረግ፤ እርዳታ አሰባስባ ልካለች። እንዲሁም በአገልግሎት ላይ የዋሉ፤ ለሐኪም ቤት የሚሆኑ ፹ አልጋዎች፤ ፹ ኮመዲኖች፤ ፲፭ የደካሞችና የበሽተኞች መግፊያ ጋሪዎች (Wheelchair) ፩ የሊጥ ማቡኪያ፤ ፩ ለጥርስ ሕሙማን መመርመሪያ የሚሆን ወንበርና፤ ብዛት ያላቸው፤ ወደ ኢትዮጵያ ከገቡ በኋላ፤ ከፍተኛ አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ የኤሌክትሮኒክስ ቁሳቁስ እቃዎች፤ ለብረታብረትና ለእንጨት የሚሆኑ ቀለሞች በሁለት ታላላቅ የእቃ መጫኛዎች ተሞልተው፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ላቋቋመችው ለእርዳታ ማስተባበሪያ ኮሚሽን ተልከዋል።


ከዚህ ላይ አንዳንድ ወገኖቻችንን የምናሳስበው፤? በወገን ስም የተሰበሰበውን ገንዘብ ለሌሎች ድርጅቶች ከማስረከብ ይልቅ፤ ሀገር በቀል በሆኑ ድርጅቶች በኩል እንዲደርስ ማድረጉ ተገቢ እነደሆነ ነው። ወገን ያልታመነ ማን ይታመናል።? ራሱን የማያምን ካለ ራሱን ይሰርቃል ማለት ነው። አለበለዚያም „ ሌባ እናት ልጅዋን አታምንም“ የሚለው የአባቶች ዘይቤ በዚህ ትውልድ ላይ እንደተፈጸመ አጠያያቂ አይሆንም።

## ፯/ የሀገረ ስብከት ጽ/ቤት መቋቋም

ከዛሬ ፳ ዓመት በፊት ለመጀመሪያ ጊዜ የተቋቋመው አንድ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ነበር፤ በአሁኑ ጊዜ ግን በ፬ ታላላቅ ከተማዎች ራሳቸውን የቻሉ የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ሲቋቋሙ፤ በ፯ ከተማዎች ደግሞ መንፈሳዊ አገልግሎት ይሰጣል። በዚህም ዓመት የእሽቱትጋርትና የኑርንበርግ የሰንበት ት/ቤቶች ወደ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ደረጃ የሸጋገራሉ። የቤተ ክርስቲያን ዕድገት እየጨመረ ከሄደ ዘንድ ማዕከላዊ አስተዳደርን መመሥረት አስፈላጊ ሁኖ ተገኝቷል። ከዚህም የተነሣ የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት አሰተዳዳሪዎች፤ የምእመናንና የሰንበት ት/ቤቶች ተጠሪዎች አባላት የሚገኙበት የሀገረ ስብከት ም/ቤት ታኅሣሥ ፯ ቀን ፲፱፻፺፫ (16.12.2000) ዓ. ም. በኮለኝ ከተማ ተመሥርቷል።

## <u>መደምደሚያ</u>


በአሁኑ ጊዜ በጀርመን ያሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታዮች እስከ ፭ ሺህ ይደርሳሉ ተብሎ ይገመታል። እነዚህ ሁሉ በቃለ ዐዋዲው መሠረ ት በሰበካ ጉባኤ አባልነት ተመዝግበው፤ ቤተ ክርስቲያን አቋቁመው መንፈሳዊ አገልግሎት ያገኛሉ ብሎ መናገር ባይቻልም፤ በዓበይት በዓላት፤ በክርስትና፤ በሥርዓተ ጋብቻና በቀብር ሥነ ሥርዓት የእግዚብሔርን ቃል የሰሙ፤ የቤተ ክርስቲያናቸውን ቡራኬ ያገኙ እጅግ ብዙ፤ የብዙ ብዙ ናቸው። በተለይም በመንፈስጭንቀት፤ በርኩስ መንፈስ ለሚሰቃዩ ወገኖች ቤተ ክርስቲያን የተስፋ አለኝታ መሆኗን፤ በየጊዜው ለመረዳት ችለናል። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ኃይል በሀገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን፤ በውጭ ሀገርም እየታየ ነው። የውጭ ሀገር ሰዎችም የቤተ ክርስቲያኒቱን መንፈሳዊ ኃይልና ፍጹም ጸጋ ከዕለት ወደ ዕለት እየተረዱት በመሄድ ላይ ናቸው። እስካሁን አያሌ ዐውደ ጥናቶች ተካሂደው ጥልቀትና ስፋት ያላቸው ትምህርቶች ተሰጥተዋል። እንደ እውነቱ ከሆነ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ገና ለጥናት የሚሆን ምሥጢራዊ መስክ ስለ አላት በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ያሉ ሊቃውንት እየፈለፈሉ የሚያወጡት እጅግ ብዙ ብዙ ነው። በውጭ ሀገር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በመቋቋሙ፤ አውሮፓውያን ምሁራን ወደ ኢትዮጵያ ሂዶ ጥናት ማካሄድ ሳያመቻቸው ሲቀር፤ በአሉበት ቦታ ሁነው ዕድሉን በሰፊው ይጠቀሙበታል። ሰለዚህም „የጥንት ክርስቲያኖች፤ የጥንት ሕዝቦች“ የሚለው አነጋገራቸው የመንፈስ ጥንካሬን እየሰጠን ነው። ለወላጆቻችን ምስጋና ይግባቸውና፤ በአካባቢው ከነበረውና ካለው የተንባላት መድበል ተለይተው፤ እንዲህ የሚያኮራ ታሪክ ስላቆዩልን፤ በውጭ ሀገር ላለን፤ በድርቅና በረሀብ፤ በጦርነትና በስደት የተጎሳቆለች ሀገር ዜጋዎች ለሆነው ሁሉ ማካካሻ የሞራል ጥገና አግኝተንበታል። ይህን የምትል አንተ ብቻ ነህ የምትሉ ካላችሁ፤ ዋቢና ጠበቃ ይገዤ መቅረብ እችላለሁ። ምንም እንኳን ከድኅነት አዘቅት ውስጥ እስካሁን መውጣት ባንችልም፤ ቤተ ክርስቲያናችን በጀርመን ሀገር የተቋቋመችው፤ ኢትዮጵያዊ ሰብእና ከሕይወት ወደ ሞት፤ ከክብር ወደ ኃሣር፤ ከልምላሜ ወደ ጉስቁልና በወረደበት ጊዜ ሰለነበር፤ የ፳ኛው ዓመት መታሰቢያ ከዚያ የመከራ ዘመን ጋር የተያያዘ ታሪካዊ ሂደት አለው።



በጀርመን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የተቋቋመችው፤ በሀገራችን ሰላም ጠፍቶ ጦርነት በተሰፋፋበት፤ የዕለት ጉርስ ጠፍቶ የሞት ጥላ ባጠላበት ጊዜ ስለዜ ስለል ጊዜ ስለ ጠለ በረከትና ስለ ሰላም ትጸልያለች። የቤተ ክርስቲያን ዋና ዓላማ ስለ ሰላም መጸለይና አብሮ ተቻችሎ መኖርን ማስተማር ነው። የቤተ ክርስቲያን የሥራ ዘርፍ ብዙ መሆኑ ቢታወቅም „ሰላም ለኩልክሙ“ (ዮሐ.፳፥፲፱ ) ሰላም ለሁላችሁ ይሁን የሚለው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትእዛዝ በጸሎተ ቅዳሴ ከ፲፩ ጊዜ በላይ በካህኑ አንደበት ይታወጃል። „የሰላም ሰው“ በመባል የሚታወቀው ማኀተማ ጋንዲ ከዕለታት በአንዱ ቀን ስለ ፍቅር ሲናገር „ሰዎች እግዚአብሔር ፍቅር ነው“ ይላሉ። እኔ ግን „ፍቅር እግዚአብሔር ነው“ እላለሁ፤ እንዳለዉ ሁሉ እኛስ በጀርመን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የተቋቋመበትን ፳ኛ ዓመት ስናዘክር፤ „ሰዎች እግዚአብሔር ሰላም ነው“ ይላሉ። እኛ ግን „ ስላም እግዚአብሔር ነው“ ብንል ተሳሳትን ይሆን? አይመስለኝም። ያውስ ቢሆን ካህኑ በጸሎተ ወንጌልና በሠርሆተ ሕዝብ ጊዜ „እግዚአብሔር የሀሉ ምስሌክሙ“ እግዚአብሔር ከናንተ ጋር ይሁን ሲል እኮ፤ ሰላም እግዚብሔር ነው ለማለት ነው። አሁንም የእግዚአብሔር ሰላም ለሁላችን፤ ቸርነቱም ለሀገራችን ይሁን፤

## የወደፊት ራእይ

„የ፳ ዓመት ሐዋርያዊ ጉዞ በምዕራብ አውሮፖ“ በሚል ርእስ ለመጻፍ ስነሣሣ ይህን ያህል ይረዝማል የሚል ግምት አልነበረኝም። ነገር ግን „ነገር ነገርን“ እየወለደ እንዲህ ሊረዝም ችሏል። ታዲያ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ መጭውንም ራእይ ሳይጠቅሱ ማለፉ ተገቢ መስሎ አልታየኝም። ከጀመሪያው ላይ ያፈውን ያላስታወሰ ለዛሬ፤ ዛሬንም በሥራ ያልተረጎመ ለነገ ሊሆን እንደማይችል ጠቅሼ ነበር። ታዲያ የትናቱና የዛሬው፤ „አጭር“ ነገር ግን „ረጅም“ በሆነው ጉዟችን በመጠኑ ተገልጿል። በነገው ራእይ የምንመለከታቸው ሁለት ዓበይት ዓላማዎች ከፊታችን ተደቅነዋል። ፩ኛ በጀርመን የሚገኘውን ሀገረ ስብከት በመንበረ ጵጵስና ደረጃ ማዋቀር፤ ፪ኛ አንድ ኢትዮጵያዊ ገዳም ማቋቋም ነው። በእነዚህ ሁለት ተቋማት ሁለንተናዊ የሆነው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትውፊት ተጠብቆ፤ በአውሮፓ ክፍለ ዓለም ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና የሃይማኖቱም ተከታዮች ለሆኑት ሁሉ እንደ ድልድይና እንደ ምሰሶ ሁነው ሊያገለግሉ ይችላሉ። ለሁለቱ ሀገሮች በረከትን ያስገኛሉ፤ ግንኙነትንም ያጠናክራሉ። ዓለም እየጠበበች እንጂ እየሰፋች አትሄድምና፤ ከአሁኑ የሚታሰብበት ክቡር ዓላማ ነው።



ነቢዩ ዳዊት በ፻፴፪ኛው መዝሙሩ „ ወንድሞች በኅብረት ቢኖሩ እነሆ መልካም ነው፤ እነሆም ያማረ ነው።“ ብሎ እንደተናገረው፤ ኅብረቱ ካለ፤ በሥራ መተርጎሙ ከባድ አይሆንም። የቻይናዎችን ምሳሌ መጥቀሱ አባባላችንን ስለሚያጠናክር፤ በሥራም እየተገለጸ በመሄድ ላይ ስለሆነ፤ ከዚህ ላይ መጥቀሱ ተገቢ ይመስለኛል። ቻይናዎች „ወንድሞች ከተባበሩ ተራራዎች ሜዳዎች፤ ሜዳዎችም ተራራዎች ይሆናሉ “ ይላሉ። ታዲያ እነዚያ የሩቅ ምሥራቅ ሰዎች ኮንፉሳውያን፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ፲፯ ቁጥር ፳ ላይ „እውነት እውነት እላችኋለሁ፤ የሰናፍጭ ቅንጣት የሚያህል ሃይማኖት ቢኖራችሁ፤ ይህን ተራራ፤ ከዚህ ወደዚያ እለፍ ብትሉት ያልፋል፤ የሚሳናችሁ ነገር የለም።“ ሲል የተናገረው ገብቷቸው ይሆን?! እምነት፤ ተስፋ፤ ፍቅርና ኅብረት ያስፈልጉናል። ካጣናቸው ብዙ ጊዜ ሆኗልና።

*ውድ ኦርቶዶክሳውያንና ኦርቶዶክሳውያት! የተከበራችሁ ምእመናንና ምእመናት!*

በዚህ ፳ ዓመት ሐዋርያዊ ጉዞ ውስጥ የተከናወኑ መንፈሳዊና ማኅበራዊ ኑሮ ነክ የሆኑ ድርጊቶች ሁሉ ከሞላ ጎደል ተወስተዋል። ውጤቱስ እስከምን ድረስ ነው? እንል ይሆናል። በአሁኑ ጊዜ የትዕግሥትን ፍሬ እየቀመስን፤ ውጤቷን በማጣጣም ላይ ነን። ከ፳ ዓመት ሐዋርያዊ ጉዞ በኋላ በጀርመን ሀገር የምንኖር ምእመናንና ካህናት ኦርቶዶክሳዊት ሕይወትን መኖር ጀምረናል። በየቦታው መንፈሳዊ አገለገሎት ይሰጣል። ከጀርመን አልፎ በጎረቤት ሀገሮች የሚሰጠው አገለግሎት እንደቀጠለ ነው። የዛሬ ፳ ዓመት ክርስትና የተነሡ ሕፃናት፤ አሁን አድገው፤ ተምረው ለመጸለይና ለመዘመር ሲችሉ፤ ከዛሬ ፳ ዓመት በፊት በአሉባልታ ከእናት ቤተ ክርስቲያናቸው ርቀው የነበሩ ተመልሰው ሲመጡ፤ የዛሬ ፳ ዓመት ቤተ ክርስቲያኑ ተባርኮ ታቦተ ቅዱስ ሚካኤል ሲገባ ቁመው የተቃውሞ ወረቀት ሲበትኑ ከነበሩት መካከል በንስሐ ተመልሰው፤ ልጆቻቸውን ክርስትና ሲያሥነሡ፤ ጸሎተ ፍትሐት ሲያስደርሱ፤ ሐሰት ወደ እውነት ተለውጦ፤ በየቦታው መንፈሳዊ አገልግሎት ለማግኘት፤ ብሎም ቤተ ክርስቲያን ለማቋቋም የሕዝበ ክርስቲያኑ ትብብር ሲታይ፤ ጌታ ለደቀመዛሙርቱ „በትዕግሥታችሁ ነፍሳችሁን ገንዘብ ታደርጋላችሁ።“(ሉቃ.፳፩፥፲፱) ያለው አምላካዊ ቃል በመፈጸሙ ለቸሩ ጌታ ለአምላከ ቅዱስ ሚካኤል የምናቀርበው ምስጋና ጥልቅ ነው። ከዚህ ላይ ቅዱስ ሚካኤልን ያነሣሁበት አንድ ምክንያት አለኝ። ነቢዩ ዳንኤል በስደት ሀገር በፋርስ ባቢሎን በነረበት ጊዜ፤ የተራዳው ሊቀ መላእክት ቅዱስ ሚካኤል

ስለነበር „ከመላእክት አለቆች አንዱ ሚካኤል እኔን ለመርዳት “ መጣ ሲል ተናግሯል። (ዳን.፲፤፲፫) አሁንም የሰአሊ ምሕረት የአምላክ አበጋዝ የቅዱስ ሚካኤል አማላጅነትና ረዳትነት አልተለየነም፤ አይለየን።

**የተከበራችሁ ክርስቶሳውያንና ክርስቶሳውያት! ውድ ወገኖቻችን!**

በዚህ ፳ ዓመት ውስጥ በጸሎት፤ በሐሳብ፤ በገንዘብ፤ በጉልበት፤ በአገልግሎት፤ በሰሚናርና በክብረ በዓላት ዝግጅት ለረዳችሁ፤ የሰበካ ጉባኤ አስተዳደር አባላት በመሆን ክርስቲያናዊ ግዴታችሁን ለተወጣችሁ ሁሉ በቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን፤ በአበው ካህናት፤ በወንድሞች ዲያቆናት፤ በሰበካ ጉባኤ አስተዳደር አባላትና በራሴም ስም ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። እንዲሁም በዚህ ፳ ዓመት ውስጥ ያለማቋረጥ ለረዱን ለኦርቶዶክሳውያን፤ ለጀርመን ወንጌላዊት፤ ለሮማ ካቶሊካዊት አብያተ ክርስቲያናት፤ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች፤ በቀና መንፈስ ተነሣሥተው ለረዱን፤ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን ወዳጆች ለሆኑ ግለሰቦች ሁሉ፤ በእናንተና በእኔም ስም እንዳመሰግን ፍቀዱልኝ።

***እንኳን ለ፳ኛው ዓመት ክብረ በዓል አደረሳችሁ።***

***እግዚአብሔር አምላክ አግልግሎታችንን ይባርክ፤ ቤተ ክርስቲያናችንንና ማኀበራችንን ያስፋ፤ አንድነታችንን ይጠብቅ!***

ሊቀ ካህናት ዶ/ር መርዓዊ ተበጀ
በጀርመን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ኃላፊ



Äthio-Deutsch Familientreff **የኢትዮጵያ ጀርመን ቤተ ሰብእ ግንኙነት**